CDTFA

# ካሊፎርንያ ውስጥ ሽያጭ ማካሄድ

## ስለ ካሊፎርንያ የግብርና የክፍያ አስተዳደር መምሪያ የተመለከተ መግቢያ



California Department of Tax and Fee Administration (የካሊፎርንያ የግብርና የክፍያ አስተዳደር መምሪያ ,CDTFA) ካሊፎርንያ ውስጥ 41 የግብርና የክፍያ ፕሮግራሞችን ያስተዳድራል። ተልዕኳችን ወሳኝ የሆኑ የህዝብ አገልግሎቶችን የሚደግፍ ገቢን በአግባቡና በብቃት በመሰብሰብ የካሊፎርንያውያንን ህይወት የተሻለ ማድረግ ነው። እርስዎንም ሆነ አዲሱን የንግድ ስራዎን በደስታ እንቀበላችኋለን። ግዛታችን የበለጸገ የስራ ፈጣሪዎች እና የብልጽና ስራዎች ታሪክ ያለው እንደመሆኑ ለሁላችሁም ዕኩል ስኬትን እንመኝላችኋለን። ይህ ህትመት በካሊፎርኒያ ውስጥ ሽያጭ በሚያከናውኑበት ጊዜ እርስዎን የሚመለከቱ አንዳንድ የህግ መስፈርቶችን ለማቅረብ እንደ ፈጣን መመሪያ ሆኖ ያገለግላል። የግዛቱ የንግድ ሥራ ሕጎች እና የግብር ሕጎች ውስብስብ ከመሆናቸው አንጻር ይህ ሁሉን አጠቃሎ የያዘ መመሪያ አይደለም። እዚህ ያለነው ለማንኛውም ሊኖሩዎ ከሚችሉ ከንግድ ስራ ግብር ጋር ተያያዥነት ላላቸው ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ነው። ብዙ ሰራተኞቻችን ከእንግሊዘኛ ውጭ ሌሎች ቋንቋዎችን የሚናገሩ በመሆኑ በቅድሚያ በሚቀርብ ጥያቄ የእርስዎ ቋንቋ ተናጋሪ የሆነ ሰው ተገኝቶ እርዳታ እንዲያደርግልዎ ለማድረግ የተቻለንን ጥረት እናደርጋለን።

## የካሊፎርንያ የሻጭ ፍቃድ

የካሊፎርንያ የሻጭ ፍቃድ ዕቃዎችን በጅምላ ወይም በችርቻሮ ደረጃ እንዲሸጡ ያስችልዎታል። የሻጭ ፍቃድ የሚያገኙት እኛ ጋር ሲመዘገቡ ነው። በአጠቃላይ በካሊፎርኒያ ውስጥ ሸቀጦችን፣ ተሽከርካሪዎችን ወይም ሌሎች እቃዎችን በህጋዊ መንገድ ለመሸጥ እና/ወይም ለማከራየት የሻጭ ፈቃድ ማግኘት አለብዎት። ልክ በአብዛኛው እንደ የገና ዛፍ ወይም የዕደ ጥበብ ዕቃዎች ሽያጭ ላይ እንደሚሰራው ሁሉ ከ90 ቀናት በላይ የሚቆይ ሽያጭ የሚያከናውኑ ከሆነ ለጊዜያዊ የሻጭ ፍቃድ ማመልከት አለብዎት።



## የሻጭ ፍቃድ ከመልሶ ሽያጭ የምስክር ወረቀት ጋር ሲነጻጸር

የሻጭ ፍቃድ እና የመልሶ ሽያጭ የምስክር ወረቀት ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው። የሻጭ ፍቃድ ካሊፎርንያ ውስጥ እንዲሸጡ የሚያስችልዎ ሲሆን በአንጻሩ የመልሶ ሽያጭ የምስክር ወረቀት ግብር ሳይከፍሉ ለአቅራቢዎችዎ የሚሸጧቸውን ዕቃዎች እንዲገዙ ያስችልዎታል። አንዴ የሻጭ ፍቃድ ካገኙ በኋላ ለአቅራቢዎችዎ በመደበኛ የንግድ ስራ ሂደት ውስጥ እርስዎ የሚሸጧቸውን ዕቃዎች እንዲገዙዎ የመልሶ ሽያጭ የምስክር ወረቀት ሊሰጧቸው ይችላሉ። የሻጭ ፍቃድ *የመግዣ ፍቃድ አይደለም*። አሁንም በንግድ ስራዎ ውስጥ ከመሸጥ ይልቅ በሚጠቀሙባቸው ዕቃዎች ላይ (ለምሳሌ፡ የቢሮ እቃዎች) ላይ ግብር መክፈል ይኖርብዎታል።

## ለሻጭ ፍቃድ ማመልከት

ለሻጭ ፈቃድ ማመልከት ነፃ ነው። ለሻጭ ፍቃድ የድረገጻችንን *የኦንላይን የአገልግሎቶች* ክፍልን በ *www.cdtfa.ca.gov* በመጎብኘት ሊያመለክቱ ይችላሉ። ማመልከቻዎን ለመሙላት የባንክ ሂሳብ ዝርዝሮችን እና የሚገመት ገቢን ጨምሮ ሥለ የንግድ ስራዎ የተመለከተ መረጃ መስጠት ይኖርብዎታል። የንግድ ስራዎን ገዝተውት ከሆነ የቀድሞ ባለቤቱን ስም እና የCDTFA የሻጭ ፍቃድ ቁጥሩን መስጠት ይኖርብዎታል። መመሪያ ካስፈለገዎ እባክዎ ለደንበኛ አገልግሎት ማዕከላችን በ1-800-400-7115 (TTY:711) ይደውሉ እና የCDTFA ተወካይ በደስታ ይረዳዎታል። አንዴ ማመልከቻውን በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ሞልተው ካስገቡ በኋላ የሻጭ ፍቃድዎን በንግድ ስራዎ የመስሪያ ቦታ ላይ ለማሳያነት ለመለጠፍ ማተም/ፕሪንት ማድረግ ይችላሉ። ለሻጭ ፍቃድ በተጨማሪም በአካል ወደ የአካባቢዎ የCDTFA የመስክ ጽህፈት ቤት በመሄድ ሊያመለክቱ ይችላሉ። የጽህፈት ቤት ስልክ ቁጥሮችን እና አድራሻዎችን ከድረገጻችን ላይ በ *www.cdtfa.ca.gov/office-locations* ማግኘት ይችላሉ።

## የግብር ማወራረጃ/ ክሊራንስ/ ይጠይቁ

እራስዎን በሚገዙት የንግድ ድርጅት መክፈል ከነበረበት ማንኛውም የሽያጭ ወይም የመጠቀሚያ ግብር ለመከላከል ለእኛ በመጻፍ የግብር ማወራረጃ/ ክሊራንስ/ እንድንሰጥዎ መጠየቅ አለብዎት። በጽሁፍ ጥያቄዎ ውስጥ የሚከተሉትን ማካተት አለብዎት፡

- የገዢው ስም፣ አድራሻ እና ስልክ ቁጥር።
- የሻጩ ስም፣ አድራሻ እና ስልክ ቁጥር።
- የንግድ ድርጅቱ አድራሻ።
- ከግዢው ዋጋ መጠን ጋር የሽያጭ ደረሰኝ ወይም የግዢ ስምምነት ግልባጭ።
- ተፈጻሚ ከሆነ፣ የሶስተኛ ወገን ኩባንያ ስም እና የመለያ ቁጥር።
- የንግድ ድርጅቱ የተገዛበት ቀን።

## የሻጭ ፍቃድ ያዦች ግዴታዎች።

የሻጭ ፍቃድ ሲኖርዎት:

- እንዴት የሽያጭና የመጠቀሚያ ግብር በንግድ ስራ እንቅስቃሴዎ ላይ ተፈጻሚ እንደሚሆን መረዳት አለብዎት።
- ሽያጭና ግዢዎችዎን የሚመዘግቡባቸው በቂ መዝገቦችን ማስቀመጥ አለብዎ (*ከታች የመዝገቦች አያያዝን ይመልከቱ*)።
- የየወቅት ሽያጮችና የመጠቀሚያ ግብር ተመላሾችን እኛ ጋር ማስመዝገብ አለብዎ። ለሻጭ ፍቃድዎ አንዴ የኦንላይን ምዝገባዎን ከሞሉ በኋላ በሚገመቱ ሽያጮች ላይ ተመስርቶ ወርሀዊ፣ የዕሩብ ዓመት ወይም ዓመታዊ የማስመዝገቢያ መርሀግብር ይሰጥዎታል።
- ማንኛውንም በሽያጭዎችዎና ግዢዎችዎ ላይ የሚከፈል የሽያጭ ወይም የመጠቀሚያ ግብር መክፈል አለብዎ።

## የመዝገቦች አያያዝ

ቢያንስ የአራት ዓመታት ትክክለኛውን የግብር ገንዘብ መጠን የሚያሳዩ መዝገቦችን መያዝ አለብዎ። መያዝ ያለብዎ መዝገቦች ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ:

- እንደ ጠቅላላ ሌጀር እና ጆርናሎች ያሉ ገቢዎን እና ወጪዎችዎን አጠቃለው የሚያቀርቡ የሂሳብ መዝገቦች። ይህን መረጃ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ሊያስቀምጡት ይችላሉ።
- እንደ ክፍያዎች፣ መቀበያ ደረሰኞች፣ ደረሰኞች፣ የስራ ማዘዣዎች፣ ውሎች ወይም ሌሎች ሰነዶች ያሉ በሂሳብ መዝገቦችዎ ላይ መመዝገብዎን የሚደግፉ ዋና መዝገቦች።
- የግብር ተመላሾችዎን ለማዘጋጀት የሚያገለግሉ ሰነዶች እና ወርክሺቶች።
- ከደንበኞችዎ የሚቀበሏቸው የመልሶ ሽያጭ የምስክር ወረቀቶች።

## መዝገቦችዎ የሚከተሉትን ማሳየት አለባቸው፡

- ከዕቃዎች ሽያጭና ኪራይ የሚገኝ ገቢን እና ከግብር ነጻ እንደሚሆን የሚያስቡትን ገቢ ጨምሮ ከሁሉም የንግድ ስራዎችዎ ያገኙትን ጠቅላላ ገቢ።
- ሁሉንም በግብር ተመላሾችዎ ላይ የሚጠይቋቸውን ተቀናሾች።
- የሁሉም የገዟቸው እቃዎች ጠቅላላ የግዢ ዋጋ።

## ለንግድ ስራዎ የሚጠየቁ ተጨማሪ መስፈርቶች።

ለሻጭ ፍቃድ ከመመዝገብ በተጨማሪ ለሌሎች እኛ ለምናስተዳድራቸው የግብርና ክፍያ ፕሮግራሞች መመዝገብ ሊኖርብዎት ይችላል (ለምሳሌ፡ የካሊፎርኒያ የጎማ ክፍያ፣ የኤሌክትሮኒክስ ቆሻሻ መልሶ ጥቅም ላይ የሚውል ክፍያ ወይም የሲጋራ እና የትምባሆ ፈቃድ ፕሮግራም)። የንግድ ስራዎን ለማከናወን በተጨማሪም ሌሎች የንግድ ፍቃዶች፣ ፍቃዶች ወይም ሰነዶችን ማግኘት ሊኖርብዎ ይችላል። የCalGold ድረገጽ www.calgold.ca.gov እንደ መጀመሪያ ለንግድ ስራዎ ተገቢውን የፍቃድ መረጃ ለማግኘት ተመራጭ ቦታ ነው። የንግድ ምክር ቤቶች፣ የኢኮኖሚ ልማት ድርጅቶች እና የንግድ ድርጅቶችም ጥሩ የመረጃ ምንጮች ናቸው። ብዙውን ጊዜ የከተማ ወይም ካውንቲ የንግድ ፍቃድ መምሪያ ሊረዳዎ ይችላል፤ ወይም እርዳታ ለማግኘት ሊደውሉልን ይችላሉ።

## የግብር ከፋዮች መብቶች ጠበቃ

እንደ የካሊፎርንያ ግብር ከፋይነትዎ እንደ የሚስጥራዊነት መብት፣ በፍትሀዊ አኳኋን የመስተናገድ መብት እና እኛ በምንወስዳቸው እርምጃዎች ላይ ይግባኝ የማለት መብት ያሉ ብዙ መብቶች አሉዎት። ችግሮችን በመደበኛ የCDTFA መስመሮች እገዛ መፍታት ካስፈለግዎ፣ ወይም በየትኛውም በእኛ በሚተዳደሩ የግብር ወይም ክፍያ ፕሮግራሞች ስለተሰጡዎ መብቶች ተጨማሪ ማወቅ ከፈለጉ ለግብር ከፋዮች መብቶች ጠበቃ ጽህፈት ቤታችንበነጻ ጥሪ መስመር 1-888-324-2798 ሊደውሉ ይችላሉ።

## ለተጨማሪ መረጃ

የአስተርጓሚ እገዛ ማግኘት ካስፈለገዎ እባክዎ ለአካባቢዎ የCDTFA ጽህፈት ቤት ይደውሉ። ፍላጎትዎ ከሆነ የራስዎን አስተርጓሚ ይዘው ሊመጡ ይችላሉ። ከእርስዎ ጋር በግልጽ ለመግባባት የተቻለንን ጥረት እናደርጋለን። አገልግሎቶቻችንን እንዴት ማሻሻል እንደምንችል አስተያየት ካልዎት እባክዎ ያሳውቁን።

ይህ እትም ሕትመቱ በተጻፈበት ወቅት በሥራ ላይ ያሉትን ሕጎችን እና ተፈጻሚነት ያላቸውን ደንቦችን አጠቃሎ ያቀርባል። ሆኖም ከዚህ ጊዜ በኋላ በህጉ ወይም ደንቦች ላይ ለውጦች ሊደረጉ ይችላሉ። በዚህ ዕትም ጽሁፍ እና በህጉ መካከል ግጭት ከተፈጠረ ውሳኔዎች በዚህ ዕትም ላይ ሳይሆን በህጉ ላይ ተመስርተው ይተላለፋሉ። ◀

